**ፀሐይ ባንክ አ.ማ. እና ዳይናሚክ ማይክሮ ፋይናንስ በጋራ ለመስራት የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረሙ**

ስምምነቱን የፀሐይ ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ያሬድ መስፍን እና የዳይናሚክ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ በዕውቀቱ አላምረው ተፈራርመዋል፡፡

የመግባቢያ ስምምነቱ ፀሐይ ባንክ በጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ሥራ እንዲሁም በግብርና መስክ የተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለመድረስ የሚያስችለው መሆኑን የፀሐይ ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ያሬድ መስፍን ገልጸዋል፡፡

በዚህም ፀሐይ ባንክ በዳይናሚክ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አማካኝነት የዲጂታል ባንኪንግ፣ የኤጀንት ባንኪንግ እና የብድር አቅርቦት ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ለመስጠት እንደሚችል አቶ ያሬድ ጠቁመዋል፡፡

የዳይናሚክ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ በዕውቀቱ አላምረው በበኩላቸው ተቋሙ በአዲስ አበባ፣ አማራ እና ኦሮሚያ ክልሎች 30 ቅርንጫፎችን በመክፈት በተለይም በጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ሥራ እንዲሁም በግብርና መስክ የተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ለማድረግ እየሠራ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

ተቋሙ ከፀሐይ ባንክ ጋር በቅንጅት እየሠራ እንደሚገኝና እስካሁን ከ18 የባንኩ ቅርንጫፎች ጋር ትስስር መፍጠሩን ገልጸዋል፡፡

የመግባቢያ ስምምነቱ በሁለቱ ተቋማት መካከል ያለውን ትብብር የበለጠ ለማጠናከርና የባንኩን የደንበኞች ቁጥር እንዲሁም የተቀማጭ ገንዘብ መጠን ለማሳደግ እንደሚያግዝ ጠቁመዋል፡፡

ዳይናሚክ ማይክሮ ፋይናንስ በሚንቀሳቀስባቸው አካባቢዎች ፀሐይ ባንክ የመደበኛ እና ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት የሚሰጡ ተጨማሪ ቅርንጫፎች በመክፈት የበለጠ ተደራሽ መሆን እንደሚችልም ተናግረዋል፡፡

በፊርማ ስነ-ስርዓቱ ወቅት የዳይናሚክ ማይክሮ ፋይናንስ የቦርድ አመራሮችና የቦርድ ዳይሬክተሮች እንዲሁም የፀሐይ ባንክ ከፍተኛ የሥራ አመራሮች ተገኝተዋል፡፡

**ፀሐይ ባንክ**

**ለሁሉ!**